ኢትዮጵያ

የሰብአዊ መብቶች አያያዝ የየሀገሩ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/ ማርች 6 ቀን 2007 ዓ.ም. በዴሞክራሲ በሰብአዊ መብቶች እና ሠራተኛ ጉዳይ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ፡፡

ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና በገዥው በኢህአዴግ ጥምር ፓርቲዎች የምትመራ ፌደራላዊ ሬፑብሊክ የሀገሪቷ ሕዝብ ቁጥር በግምት 77 ሚሊየን ነው፡፡ በ2005ቱ ጁን የምክር ቤት ምርጫ ኢሕአዴግ በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ሀገሪቷን ለአምስት አመት ለማስተዳደር አሸንፏል፡፡ የሃገር ውስጥና አለም አቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው እዚያና እዚህ አንዳንድ ጉድለቶች ቢታዩበትም ባጠቃላይ በትክክለኛና ባስተማማኝ ሁኔታ የተካሄደ እንደነበር የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

ፖለቲካ ፖርቲዎች በአመዛኙ በብሔር ብሔረሰብ የተደራጁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ተቀዋሚዎች ቀስ በቀስ የጥምር ፓርቲ የመመሥረት ሂደት አሣይተዋል፡፡ የመንግስት ባለሥልጣናት በፀጥታ ኃይሎች ላይ የተዋጣለት ቁጥጥር እያደረጉ ሣለ በፀጥታ ኃይሎች የታቀፉ አንዳንድ ግለሰቦች መንግስት ከፈቀደላቸው መመሪያ ውጪ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ባመቱ ውስጥ የተዘገቡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የሚከተሉትን ድርጊቶች ያካተቱ ነበሩ፡፡ በቅርብ በተካሄዱ ምርጫዎች መንግስታቸውን ለመለወጥ የፈለጉ ዜጐችን መብት መገደብ፣ የሕግ ድጋፍ ሣይኖር ሰዎችን መደብደብና መግደል፣ ያለምክንያት የሰውን ክብር ለመንካትና በማቆያ ቤት ያሉ ግለሰቦችንና የተቃዋሚ ደጋፊዎችን በፀጥታ ሀይሎች ያላግባብ እንዲጉላሉ ማስደረግ፡፡

ብዙ ነገር በጐደላቸው እሥር ቤቶች ውስጥ በሥር ማቆየትና ሰዎችን ሳይከሰሱ ይዞ የማሠር ተግባራት ተከስተዋል፡፡ እነዚህ ተግባራት በተለይ የተቃዋሚዎች አባላት ወይም ደጋፊዎች ሳይሆኑ አይቀርም ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ተፈጽመዋል፡፡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት ለብዙ ጊዜ በስር ላይ ቆይተዋል፡፡ የዜጎች በግል የመኖር መብትና ሕጉ ያስቀመጣቸውን የፍተሻ መመሪያዎች ደጋግሞ አለመከተል፣ በፕሬስ ነፃነት ላይ ገደብ ማበጀት፣ ያለምክንያት ሰዎችን መያዝና በሥር ማቆየት፣ መንግስትን የሚተቹ ጽሁፎችን የሚያወጡ ጋዜጠኞችን ማስጨነቅ፣ በመሰብሰብ ነፃነት ላይ ማነቆ ማበጀት፣ በማህበር የመደራጀት ነፃነት ላይ ገደብ መጣል፣ ሴቶችን ከማሕበራዊ ሕይወት ማግለልና የሕፃናትን መብት አለማስከበር፣ የሴቶች ግርዛትን አለማስቆም፣ ለኤኮኖሚ ጥቅም ማግኛነትና ለወሲብ ጥቃት ሲጋለጡ በቸልታ ማየት፣ ሰዎችን ማዘዋወር፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የሃይማኖትና የአናሣ ብሔረሰቦች በጉዳተኝነታቸውና ውሁዳን በመሆናቸው ብቻ በማህረሰቡ መድሎ ሲፈፀምባቸው ዝም ብሎ ማየትና በማህበራት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመንግስት ጣልቃ መግባት የተለመዱ ተግባራት ነበሩ፡፡

ክፍል አንድ፣

ሰብአዊ መብቶችን ማክበር የሰውን ምልኡጋት ማክበር ይህም የሚከተሉትን ያካትታል

ሀ - በዘፈቀደ ወይም ከሕግ ውጭ ሕይወትን ማሳጣት ባለፈው አመት እንደተፈፀሙት ያሉ ግድያዎች በዚህ ዓመት የፖለቲካ መንስኤ የነበራቸው ግድያዎች አልነበሩም፡፡ ይሁን እንጂ የፌደራልና ያካባቢ ፖሊስ ኃይሎች ባመቱ ውስጥ ከሕግ ውጭ ግድያዎችን ፈፅመው ነበር ፡፡

ጃንዋሪ 23 በምስራቅ ወለጋ ዞን ጉድሩ ወረዳ ወስጥ የፌደራል ፖሊስ 15 ሕዝበ ትዕይንት አድራጊዎችን ተኩሶ ሲገድል፡፡ 19 በሚሆኑት ላይ ደግሞ ጉዳት አደረሰ፡፡ ተኩስ የተከፈተው ባካባቢ የመንግስት ኃይሎችን ለመቃወም ሰልፍ በወጡ ነዋሪዎች ላይ ነው፡፡ በደረሰው አጋጣሚ ላይ የተካሄደ ምንም ዓይነት ምርመራ የለም፡፡

ማርች 6 ከስራ ውጪ የነበረና ዓለሙ ድሪባ የተባለ ፖሊስ መኮንን ካልታወቁ ግብረአበሮቹ ጋር ሆኖ በጎንደር ከተማ 4 ወጣቶችን ገድሏል፡፡ ዓለሙ የ17 ዓመቱን በረከት ፋንታሁንን፣ የ18 ዓመቱን አበበ ወንድማገኝን፣ አሁንም የ18 ዓመቱን ስንታየሁ ወርቅነህንና የ19 ዓመቱን ዳዊት ተስፋዬን ቀርቦ እጃቸውን ወደ ላይ እንዲያነሱ አዘዛቸው ይባላል፡፡ ከዚያም በ30 ያርድ ርቀት ላይ ወደሚገኝ ወንዝ ወስዷቸው፣ መሬት ላይ እንዲተኙ ካደረጋቸው በኋላ የእያንዳንዳቸውን እራስ በጥይት እየመታ ገደላቸው፡፡ ዓለሙም ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደርጐ ክስ ሣይመሠረትበት ዓመቱን ጨርሷል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ እንደዘገበው በግንቦት 27 *በኦሮሚያ* ክልል

ናዝሬት ከተማ በሱቅ ባለቤቶችና በፖሊሶች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት የተነሣ ፖሊስ ዓለሙ ተስፋዬ፣ ታሪኩ ያኪሰና መንሱር ሙሰማ የተባሉ ሰዎችን በጥይት ተኩሶ ገድሏቸዋል፡፡ ፖሊስ ከይዞታቸው ሊያስነሣቸው ሲሞክር ባለቤቶቹና ሠራተኞቻቸው በፖሊሶቹ ላይ ድንጋይ በመወርወር የአፀፋ ርምጃ ወስደዋል፡፡ የተከሰተውን ግጭት አስመልክቶ ምንም ዓይነት የማጣራት ሥራ አልተሰራም፡፡

በ2005 ኦገስት ላይ *በጊቤ* ወረዳ ኤልያስ ሞላንጐ በጦር ሰራዊት አባላት እንደተገደለ ሪፖርቶች ደርሰዋል፡፡

ኤልያስ ከተገደለ በኋላ አስከሬኑ *ለሆሣዕና* ከተማ ነዋሪዎች በግልጽ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ኤልያስ በ2000ው የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ላይ በታዛቢነት ሠርቷል፡፡ በኋላም ለገዥው ፓርቲ አሸናፊነት አጐናጽፎታል የተባለውን የምርጫ ውጤት ተቃውሞ ነበር፡፡ ስለ ግለሰቡ ግድያ የተደረገ ሕጋዊ የማጥራት ሥራ ምንም የለም፡፡

በ2005 ስለ መላው ኢትየጵያ አንድነት ፓርቲ ቅንጅት አባላት የፖለቲካ ግድያዎች በተለይ ስለ አንለይ አዲስ፣ አየልኝ ወንድምነህ፣ ጥላሁን ከበረና አላምር አእምሮ ግድያዎች ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በ2005 መጨረሻ ፖሊስ ጥላሁን ከበረን ገድለዋል የተባሉ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡ ይሁን እንጅ ከዚያ በኋላ ጉዳዩ በምን ደረጃ ላይ ተይዞ እንዳለ የሚያስረዳ መረጃ የለም፡፡ በ2005 በፖሊስ፣ በሚሊሺያና በቀበሌ ባለሥልጣናት ስለተፈፀሙ የፖለቲካ ግድያዎች እስከ ዛሬ የተሰጠ ምንም መረጃ የለም፡፡ በጊዜው 24 የኦሮሞ ኮንግሬስ ፓርቲ አባላት ተገድለዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አህመድ አደም የተባሉ ግለሰብና የምክር ቤት ተመራጭ የነበሩት የተከበሩ አቶ ተስፋዬ አዳነ ይገኙበታል፡፡ ባመቱ መጨረሻ በአቶ ተስፋዬ አዳነ ግድያ እጃቸው አለበት የተባሉ ተጠርጣሪዎች በዝዋይ ታስረው ነበር፡፡ ነገር ግን ጉዳያቸው በምርመራ ደረጃ እንደነበረ ቀረ፡፡ በ2005 በአማራ ክልል የቅንጅት ፓርቲ የምርጫ አስተባባሪ የነበረው የሀሰን እንድሪስ ግድያ ወይም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በግንቦት ወር የተገደሉት የሸክ ኡስማን ሐጂ አብደላ ጉዳይ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አይታወቅም፡፡ ሁሉቱም ግድያዎች የተፈፀሙት በቀበሌ ባለሥልጣናት ነው፡፡

ኦገስት ወር 2005 በበዘላ ሎምቢሶ ላይ በወታደሮች ስለተፈፀመው ግድያና ስለ ሚስቱ መደፈር እስከ ዛሬ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በዘላ በ2000ው የብሔራዊና የክልል ምርጫዎች ጊዜ አንድ የፖሊስ አባል ገድሏል ተብሎ ተከሶ ነበር፡፡

ሴብቴምበር 2005 የቅንጅት አባል በነበሩት በአቶ አሰፋ ጌታሁን ላይ የተፈፀመውን ግድያ፤ ኦክቶበር 2005 በግርማ ብሩ ላይ የተደረገውን የፖለቲካ ግድያ ወይም የሞሴ ዋሴና የጥላ ፀጋን ሕገወጥ ግድያ በተመለከተ ምንም ዓይነት መረጃ አልነበረም ፡፡

በ2004 በፀጥታ ኃይሎች ተገድለዋል ስለተባሉት ከዚህ በታች ስማቸው ስለተዘረዘሩት ሰዎች ግድያም ቢሆን የታየ ይህ ነው የሚባል ርምጃ አልተወሰደም፡፡ በሶማሌ ክልል የተፈፀመው የከበደ ኡዞ ግድያ፤ በኦሮሚያ ክልል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ በነበረው በአለሙ ተስፋዬ ግድያ ፤እዚያው ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት ተማሪ በነበረችው በአመለወርቅ ቡሊ ግድያ፤ በተለያዩ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አባላት ላይ የተደረጉ ግድያዎች፣ በጎዴ ከተማ በአስር ሰዎች ላይ የተፈፀመው ግድያ፤ በአማራ ክልል የተገደሉት የገለታው ማሞና በአዲስ አበባ የተገደለው ኤፍሬም አለማየሁ ገዳዮች ጉዳያቸው የት እንደደረስ አይታወቅም ፡፡

በ2005 ፖሊስ ፈፀማቸው ስለተባሉት የሰላማዊ ሰልፍ አድራጊዎች ግድያ ጉዳይም የሚታወቅ ምንም የምርመራ ውጤት የለም ፡፡ እነዚህም ግድያዎች በሰኔ ወር በአዲስ አበባ 42 ያልታጠቁ ሰዎች ግድያ ፤ በኑቬምበሩ ሁከት ላይ የተገደሉትን 46 ሰዎች፤ የተማሪ ሽብሬ ደሳለኝ ግድያ ፤ የ16 ዓመቱ ተማሪ ነቢይ አለማየሁን ግድያ፣ የሰባት ልጆች እናት የነበሩት የዙልፋ ሱሩር ግድያ እንዲሁም የአስራስድስት ዓመቶቹ መንድማማቾች የፈቃዱ ነጋሽና የአብርሃም ይልማን ግድያ ያጠቃልላሉ ፡፡ ሰባት የፖሊስ አባላትም በህዳሩ ብጥብጥ የተገደሉ ሲሆን ፤ በነሱም ግድያ ማንም ግለሰብ የተከሰሰ የለም ፡፡ በኦክቶበር መጨረሻ ላይ የአጣሪ ኮሚሽኑ በ2005 ተቃውሞ ወቅት የፀጥታ ሃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ሃይል ተጠቅመዋል የተባለውን ጉዳይ እንዲያጣራ በመንግሥት ተቋቋመ ፡፡

ኮሚሽኑ 193 ሰለማዊ ዜጎች (ቀደም ሲል በመንግስት ሪፖርት ከተደረገው ቁጥር ወደ አራት እጥፍ የሚጠጋ ነው)እና 6 የፀጥታ ሃይሎች አባላት መገደላቸውን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 763 ሰላማዊ ዜጎችና 71 የፀጥታ ሃይሉ አባላት ባብዛኛው በከባድ ሁኔታ መጎዳታቸውን አስታውቋል ፡፡

እንደወቅቱ የብጥብጥ ሁኔታም የፀጥታ ሃይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ሃይል እንዳልተጠቀሙ ኮሚሽኑ ገልጿል ፡፡ ይሁን እንጂ ሪፖርቱ ከመገለፁ ቀደም ሲል የኮሚሽኑ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ከመንግስት አካላት ማስፈራሪያና ዛቻ ደርሶብናል በሚል ከአገር ኮብልለዋል ፡፡

ከኮበለሉ በኋላም ሁለቱም በግልፅ በሕዝብ ፊት በቪዲዮ የተቀረፀ በሰኔ የተካሄደ ስብሰባን እንደመረጃ በማሳየት ኮሚሽኑ ቀደም ሲል ስምንት ሰሁለት በሆነ የድምፅ ብልጫ ተመጣጣኝ ያልሆነ ሃይል ጥቅም ላይ ውሏል ብሎ የወሰነ እንደ ነበር እንዲሁም የተገደሉትም ሆነ የተጐዱት ሰዎች ቁጥር በኋለኛው ሪፖርትም ያልተቀየረ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ከዚህ የድምፅ ብልጫ ውሳኔ በኋላ የመንግሥት ባለስልጣናት የኮሚሽኑን አባላት ውሳኔአቸወን እንዲቀይሩ ይጐተጉቷቸው እንደነበር ተናግረዋል፡፡

ባመቱ መጨረሻ ዲሴንበር 2003 እስከ ሜይ 2004 በጋምቤላ ክልል በነበረው ግጭት ወቅት በመቶ የሚቆጠሩ አኙዋኮችን የገደሉ፣ የደፈሩና ያሰቃዩ የመንግስት ወታደሮች ክስ እስካሁን ውሳኔ አልተሰጠበትም፡፡ በ2004 ይህንኑ ጉዳይ እንዲያጣራ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ ነበር፡፡ በኮሚሽኑም ግኝት መሠረት ስድስት የጦሩ አባላት በቁጥጥር ስር ውለው በግድያዎቹ ውስጥ በነበራቸው ተሳትፎ ለፍርድ ቀርበዋል፡፡

ባመቱ መጨረሻ አብዛኛው ከ1998 — 2000 *በኢትዮጵያና ኤርትራ* መሃል በተደረገው ጦርነት ወቅት በግምት ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ፈንጂዎች ባገሪቱ ውስጥ ተቀብረው ነበር፡፡ በዓመቱ ውስጥም *በኤርትራ አዋሳኝ* ቀበሌዎች 5 ሰላማዊ ዜጐች በፈንጂ ሲሞቱ 20 ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ የመንግስት ፈንጂ አምካኝ ቡድንም ፈንጂዎችን ፈልጐ በማምከኑ ሂደት የተወሰነ ስራ ሰርቷል፡፡ *በኤርትራና ኢትዮጵያ* ያለው የተባበሩት መንግስታት ልኡክ / አንሚ / ባለስልጣናት በዚያው ዓመት በኤርትራ ድንበር በሁለቱም በኩል አዳዲስ ፈንጂዎች እንደተቀበሩ ሪፖርት አድርገዋል ፡፡ መንግስትና አንሚ ድንበሩን ተከትሎ በተመረጡ ቦታዎች ፈንጂ የማምከን ሥራ ከመስራታቸውም በላይ ለነዋሪዎች የት የት ቦታ ላይ ፈንጂዎች እንደተቀበሩ መረጃ ሰጥተዋል ፡፡

የታጠቁ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር / ኦነግ/ እና የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር / ኦብነግ/ አባላት ባገሪቱ መንቀሳቀሳቸውን ቀጥለዋል፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜም በነዚህ ቡድኖችና በመንግስት ሃይሎች መሃከል የተደረጉ

ግጭቶች በውል የማይታወቅ ቁጥር ባላቸው ሰላማዊ ዜጎች፤ የመንግሥት ፀጥታ ሃይል አባላት እንዲሁም በኦነግና ኦብነግ ተዋጊዎችና ደጋፊዎች ላይ የሞት አደጋ አድርሰዋል ፡፡

ኤፕሪል 15 ላይ በኦሮሚያ ክልል በሚገኘው በጌዶ ዋነኛው ገበያ የደረሰው ፍንዳታ 15 ሰዎችን ሲገድል 37 ደግሞ አቁስሏል ፡፡ መንግስት ለፍንዳታው ተጠያቂ ያደረገው የኦሮሞ ነፃ አውጪ ሃይሎችን ቢሆንም ሁሉም እኛ አላደረግንም ብለዋል ፡፡ የኦብኮ አባላት ናቸው የተባሉትን ጨምሮ በዛ ያሉ ግለሰቦች ከፍንዳታው ጋር ተያይዞ በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ባመቱ መጨረሻም የነዚህ ሰዎች ጉዳይ ለሕግ ይቅረብ አይቅረብ ምንም ሪፖርት አልነበረም ፡፡

በዓመቱ ውስጥ በአዲስ አበባና በሌሎች ያገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ ፍንዳታዎች ሪፖርት ተደርገዋል፡፡ ግንቦት 12 በ9 በተለያዩ ፍንዳታዎች ብቻ አዲስ አበባ ውስጥ 4 ሰዎች ሲሞቱ 42 ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ የፀጥታ ሃይሎች ለፍንዳታዎቹ ተጠያቂ ያደረጉት ኦነግን ሲሆን ከኤርትራ መንግሥት ጋርም ተባብሮ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኦነግ ግን ማስተባበያ ሰጥቷል ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የታሰረም የተከሰሰም አልነበረም ፡፡

ሜይ መጨረሻ በሶማሌ ክልል በጂጂጋ ባንድ ሆቴልና በሁለት ምግብ ቤቶች በተከታታይ በደረሱ ፍንዳታዎች 42 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል ፡፡በተለያዩ ጎሳዎች ግጭት ምክንያት ባመቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል፤ ቆስለዋል እንዲሁም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ተፈናቅለዋል ፡፡(ክፍል 5ን ይመልከቱ)

ጁን 11 ታጣቂዎች ከአዲስ አበባ ወደ ጋምቤላ ይሄድ በነበረ አውቶቡስ ላይ **ጋምቤላ ክልል ውስጥ በሚገኘው በቦንጋ** ከተማ አቅራቢያ ጥቃት አድርሰዋል ፡፡ በትንሹ 14 ሰዎች ሞተው ብዙዎች ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ጥቃት አድራሾቹ ያኮረፉ የአኙዋክ ጎሣ አባላት ሳይሆኑ አይቀርም፡፡ ብዛት ያላቸው ሰዎች ከዚሁ ጥቃት ጋር በተያያዘ በቁጥጥር ሥር ውለው በግደያ ወንጀል ተከሰዋል ፡፡ ባመቱ መጨረሻ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ነበር፡፡

ሴፕተምበር 3 ጂጂጋ በሚገኘው የወንድማማቾች ሆቴል ውስጥ የእጅ ቦምብ ተወርውሮ የሆቴሉን ባለቤት ሲገድል ሌሎች ሰባት ሰዎችን አቁስሏል ፡፡ ባመቱ መጨረሻም መንግስት ተጠያቂዎችን በቁጥጥር ሥር አላዋለም ፡፡

በሴፕተምበር 15 አዲስ አበባ ውስጥ በደረሰ ፍንዳታ 3 ሰዎች ሞተዋል፡፡ መንግሥት ሶስቱም የሞቱት ግለሰቦች ቦንብ ለመስራት እየሞከሩ የነበሩ የኦነግ አባላት እንደነበሩና ቦንብ መስሪያውም ዕቃ በኤርትራ መንግሥት የተሰጣቸው ነበር ብሏል ፡፡ ይሁን እንጂ ብዙዎች የመንግሥት የፀጥታ አካላት በፍንዳታው እጃቸው እንዳለበት ያስታውቃሉ ፡፡

በአመቱ ውስጥ በሙስሊሞችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና አማኞች መሃከል የተፈጠሩ ግጭቶች ለብዙ ሰዎች መሞትና መቁሰል ምክንያት ሆነዋል ፡፡(ክፍል 2 ሐን ይመልከቱ)

በ2005 በጂጂጋ በአራት ሆቴሎችና በአንድ መኖሪያ ቤት ላይ በደረሱትና አምስት ሰዎችን ገድለው 31 ባቆስሉት የእጅ ቦንብ ፍንዳታዎች ጉዳይ ዙሪያ ምንም አዲስ ነገር አልታየም ፡፡

ስለ 2004ቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቴሌቭዥን ክፍል ፍንዳታ ተጠርጣሪ ታሳሪዎች የሕግ ሂደት ምንም ተጨማሪ መረጃ የለም፡፡ በ2004 በኦሮሚያ ክልል በደብረዘይት ከተማ ባንድ የትግራይ ተወላጅ ግለሰብ ሱቅ ላይ ስለደረሰው ፍንዳታ ጉዳይ ምንም የተሰወጠ ነገር የለም፡፡ ፖሊስ ኦነግ ለፍንዳታው ተጠያቂ ነው ይላል ፡፡ አዲስ አበባ የሚገኘው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አሁንም ከ1975-91 በነበረው የደርግ አገዛዝ ወቅት የዘር

ማጥፋት ወንጀልና ያለ ሕግ ሰዎችን በመግደል የተከሰሱትን ግለሰቦች ጉዳይ በመመልከት ላይ ይገኛል ። (ክፍል 1ሠን ይመልከቱ)

ለ. *መሰወር*

የኖቬምበር 2005ቱን ፖለቲካዊ ተቃውም ተከትሎ የተሰወሩት በእስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች እስካሁኑ የሪፖርት ወቅት ድረስ ደብዛቸው እንደጠፋ ነው ። ገለልተኛው አጣሪ ኮሚሽን የፀጥታ አካላት ከ30,000 በላይ ንፁሃን ዜጎችን ከማንኛውም ግንኙነት ውጪ 3ወር ለሚጠጋ ጊዜ በሩቅ ማቆያ ጣቢያዎች ይዘው ማቆየታቸውን ሪፖርት አድርጓል ። ሌሎች ይህ ቁጥር ከ50.000 ሊበልጥ እንደሚችል ግምታቸውን ይገልፃሉ። ባመቱ መጨረሻ ከጥቂት መቶዎች በስተቀር ሁሉም እስረኞች የተለቀቁ ሲሆን የቀሩት ችሎት ፊት ቀርበዋል። በጃንዋሪ ወር ኢሰመጉ ዲሴንበር 2005 የተሰወሩ ስድስት ሰዎች እንደነበሩ ሪፖርት አድርጓል። ዲሴንበር 2 ቀን የፀጥታ ሃይሎች በላፍቶ ክፍለ ከተማ የሚገኙትን ሻምበል አበበ አለሙና ህለተወርቅ ዘውዱ የተባሉ የአቃቂ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎችን፤ እንዲሁም የኮልፌ ክፍለ ከተማውን ወንድማገኝ ገደፋው አግተዋል። በዲሴንበር 21ና 22 ቀን ደግሞ ታደሰ ዘላለም፤ አያና ጪንዴሳ እና ለገሰ ቶሌራ የተባሉ ሰዎችን በኦሮሚያ ክልል በነቀምት ውስጥ ከሚገኘው የነቀምት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አግተው እንደወሰዱ ሪፖርት

ተደርጓል ።

በጁን 2005 በፀጥታ ሃይሎች የታገቱት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አሸናፊ ብርሃኑ፤ ፀጋዬ ንጉሴ ፤ዳንኤል ወርቁ፤ አደም ሁሴን፤ጅላሉ ተማም፤ ግሩም ሰይፉ፤ መኮንን ሰይፉ፤ እንደሻው ተረፈ፤ዳንኤል አበራ፤ተስፋዬ ባጫ፤ተስፋዬ ጀመና፤ቦንሳ በየነ፤ጌቱ በጂ፤ ሰለሞን በቀለ፤ አማኑኤል አስራት፤መስፍን መርጊያ፤ ወይም ዳዊት ደመረው የት እንደሚገኙ የሚታወቅ ነገር የለም።

በሜይ ወር የኦሮሞ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በሆነው ሜጫና ቱለማ ማህበር የጥበቃ ሰራተኛ በነበረው በጂግሳ ሶሬሳ እስር ጉዳይ ላይ ምንም ለውጥ የለም። ዛሬም በአዲስ አበባ እስር ቤት በእስር ላይ እንደሚገኝ ሪፖርት ተደርጓል።

በጁን 2005 ሶስት የኢትዮጵያ አየር ሃይል አባላት የጦር ሄሊኮፕተራቸውን ጅቡቲ ውስጥ አምቡሊ ላይ አሳረፉ። ሁለቱ መኮንኖች የፖለቲካ ጥገኝነት እንደጠየቁ ይነገራል። ይሁን እንጂ አንድ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ልዑክ በሚቀጥለው ቀን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ አሳምኗቸዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናልና የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ጂቡቲ በነበሩበት ወቅት ሊጐበኟቸው ሞክረው ተከልክለዋል። ባመቱ መጨረሻም ቤተሰቦቻቸው ላገር ውስጥ የዜና ምንጮች ፓይለቶቹ በእስር ላይ እንደሆኑ ነግረዋቸዋል። የታሰሩትም ባንድ የአየር ሃይል ማዘዣ ጣቢያ እንደሆነና ጐብኚዎችም እንዳያዩአቸው መደረጉ ተገልጿል።

ሐ. *ማሰቃየትና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ አረመኔያዊ ወይም ክብረነክ (አዋራጅ) አያያዞች ወይም ቅጣቶች*

ምንም እንኳን ሕገ - መንግስቱና ህጉ ማሰቃየትን እና ማንገላታትን ቢከለክሉም ብዙ ተአማኒ ሪፖርቶች የፀጥታ ባለስልጣናት ባብዛኛው ታሳሪዎችን እንደሚደበድቡና እንደሚያንገላቱ ይገልፃሉ። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሪፖርት አድርገዋል።

በፌብሯሪ 28 ቀን ኦብኮ የተባለው ተቃዋሚ ፓርቲ የፀጥታ ሃይሎች ከሜአ ወረዳ የክልል የፓርላማ አባል የሆኑትን አቶ ወጋየሁ ደጀኔን መደብደባቸውንና ማስፈራራታቸውን ሪፖርት አድርጓል። ይህ የሆነውም ከኦሮሚያ ክልል የካውንስል ስብሰባ በኋላ እንደነበር ተገልጿል። ባመቱ መጨረሻም ማንም ላይ ክስ አልቀረበም።

በኢሰመጉ ሪፖርት መሠረት በጁላይ 30 ላይ የፀጥታ ሃይሎች አንድ የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) እና አምስት የኦብኮ ክልላዊ የፓርላማ አባላት በሜጫና ቱለማ ጉዳይ የተቻለን ችሎት ተከታትለው ሲመለሱ ታስረው መደብደባቸው ተገልጿል፡፡ ባመቱ መጨረሻም ማንም ላይ ክስ አልቀረበም፡፡

በጃንዋሪ 23 ብዛት ያላቸው የታጠቁ ወታደሮች በኦሮሚያ ክልል የጉዱሩ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ ሰባት ሴቶችን አስገድደው መድፈራቸውን ኦብኮ ሪፖርት አድርጓል፡፡ የጥቃቱ ሰለባዎች በ18 እና 37 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ነበሩ፡፡ ባመቱ መጨረሻም ማንም በቁጥጥር ስር አልዋለም፡፡

የሜይ 2005ቱን በኦሮሚያ ክልል በሲራሮ ወረዳ የኦብኮና ህብረት ፓርቲ አባል የነበረው አብደታ ዲታ ኤንቴሌ ራሱን እንዲያጠፋ ያስገደደውን ድብደባ በተመለከተ ምንም ለውጥ አልታየም፡፡

በኦክቶበር 2005 ሪፖርት የተደረገውን የአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ፖሊሲ አማካሪና የግንቦቱን ምርጫ ሲቆጣጠር የነበረው የኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል በነበረው በአቶ ዳንኤል በቀለ ላይ የደረሰውን ጥቃት በተመለከተ ምንም ለውጥ አልታየም፡፡ ባመቱ መጨረሻም አቶ ዳንኤል በቀለ በክህደትና ዘር ማጥፋት ወንጀሎች ተወንጅሎ ፍርድ እየተከታተለ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ይገኛል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና ወላጆች ላይ በ2004 ድብደባ ባካሄዱት ፖሊሶችም ላይ ይሁን በዚያው አመት በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አባላት ላይ ጥቃት እንዳደረሱ አቤቱታ በቀረበባቸው ሚሊሺያዎች ላይ የሚመለከታቸው አካላት ምንም አይነት እርምጃ አልወሰዱም፡፡

የፀጥታ ሀይሎች በሰላማዊ ሰልፎች ወቅት ሰዎችን ይደበድባሉ፡፡ (ክፍል 2 ን ይመልከቱ)

በ2005 በሁለት የቀድሞ ባለስልጣናት (በቀድሞው አገር ውስጥ ጉዳዮችና ደህንነት ምኒስትር ተስፋዬ ወ/ሥላሴና የቀድሞው ወንጀል ምርመራ ሃላፊ በነበረው በለገሰ በላይነህ) ላይ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በደርግ አገዛዝ በማሰቃየታቸው ስላሳለፈው የሞት ፍርድ ውሳኔ ምንም አዲስ መረጃ የለም፡፡ ባመቱ መጨረሻም የሞት ፍርዱ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡

ባመቱ ውስጥ የጐሣ ግጭቶች ለመቶዎች መጐዳትና መሞት ምክንያት ሆነው ነበር፡፡ (ክፍል 5ን ይመልከቱ፡፡)

የእስርና የማቆያ ቦታዎች ይዞታ

የእስር ቤቶችና የማቆያ ቦታዎች ይዞታ በጣም መጥፎ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ የታሳሪዎች መጨናነቅም ዋነኛው ችግር ሆኖ ቀጥሏል፡፡ እስረኞች ባብዛኛው 21.5 ስኩዌር ጫማ የማይሆን የመኝታ ቦታ እስከ 200 ታሳሪ በሚይዙ ክፍሎች ይሰጣቸዋል፡፡ ለየቀኑ ምግባቸውም የሚያዘው በጀት 0.35 የአሜሪካ ብር (ሶስት ብር) ላንድ ታሳሪ ሲሆን ብዙዎቹ ታሳሪዎች ቤተሰቦቻቸው ምግብ እያመጡላቸው ወይም በራሳቸው ወጪ ካካባቢው ምግብ እየገዙ ይመገባሉ፡፡

የእስር ቤቶቹ ይዞታ ንፅህና የጐደለው ከመሆኑም በላይ የህክምና አገልግሎቱም አስተማማኝ አይደለም፡፡ ለእስር ቤቶች ዕድሳት የሚውልም በጀት የለም፡፡

በማቆያ ስፍራዎች ብዙ ጊዜ ፖሊሶች ታሳሪዎችን ይደበድቡ ነበር፡፡ ጐብኚዎች ባጠቃላይ የተፈቀደላቸው ቢሆንም አንዳንዴ ግን ይከለከሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ የታሰሩት የቅንጅት መሪዎች የመጐብኘት መብታቸው ተገድቦ የቅርብ ቤተሰቦቻቸው ብቻ ባመት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲጐበኟቸው ተደርጐ ነበር፡፡

የስታቲስቲክስ መረጃ ባይኖርም በህመም ምክንያት በእስር ቤቶች ውስጥ ጥቂት ታሳሪዎች ሞተው ነበር፡፡ የእስር ቤት ባለስልጣናት የነዚህን ሞቶች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ ከምርጫው በኋላ በተከሰተው

ብጥብጥ ምክንያት የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን በትንሹ 17 በቁጥጥር ስር የዋሉ ተቃዋሚዎች በእስር ላይ እንዳሉ መሞታቸውን አረጋግጧል፡፡

ባለስልጣናት አንዳንድ ጊዜ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን ከትልልቅ ሰዎች ጋር ያስሩ ነበር፡፡ ለእነዚህ ልጆች በወጣት አጥፊዎች ማረሚያ ቦታ ሲታጣ ነበር ከትልቆቹ ጋር የሚታሰሩት፡፡ እድሜያቸው ከ15 አመት በታች የሆኑ አጥፊዎች የሚታረሙበት የወጣት ጥፋተኞች ማረሚያ አንድ ብቻ የነበረ ሲሆን እሱም 150 አጥፊዎችን ብቻ የመቀበል አቅም ያለው ነበር፡፡

እንደሰብአዊ መብት ደርጅቶች ሪፖርት በ2005 መንግስት ባብዛኛው እድሜያቸው ከ18 እስከ 23 የሆነና በኑቬምበር 2005 በአዲስ አበባ በተካሄደው ሰፊ የቤት ለቤት ፍተሻ የታሰሩ ከ10,000 እስከ 18,000 የሚደርሱ ግለሰቦችን ቀደም ሲል ደርግ በወታደራዊ ካምፕነት ይጠቀምበት ወደነበረው ከአዲስ አበባ ምዕራብ 375 ኪ.ሜ. ወደሚርቀው ዴዴሳ ወደተባለው ቦታ አጓጉዞ ነበር፡፡ ባመቱ ውስጥ አብዛኞቹ ታሳሪዎች ተፈትተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በጥቂት መቶዎች የሚቆጠሩት በቁጥጥር ስር እንዳሉ ሲሆን ከህዳር 2005ቱ ብርበራ ጋር በተያያዘ ወንጀሎች ተከሰዋል፡፡

በጁላይ ወር 90 አልጋዎች ያሉት የሴቶች እስር ቤት ቃሊቲ ውስጥ ተመርቋል፡፡ ይሄው በእስር ቤቱ ግቢ ውስጥ ብቻውን ያለው ህንፃ የተሰራው ጀስቲስ ፎርኦል-ፕሪዝን ፌሎውሺፕ የተባለ ቤያድ ከውጭ መንግስታት ባገኘው እርዳታ ነው፡፡ ይህ ህንፃ የተሻለ የፅዳት ሁኔታ ያለው፣ ለሴቶችም የተሻለ ገመና ጠባቂ ከመሆኑም በላይ መጣበብን ይቀንሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ባመቱ መጨረሻም ለወንዶች የሚሆን አዲስ እስር ቤት ግንባታ በቃሊቲ አካባቢ እየተከናወነ ነበር፡፡

ባመቱ ውስጥ የአለማቀፉ ቀይመስቀል ኮሚቴ(ICRC) በየክልሉ ያሉትን እስር ቤቶች፣ ማቆያ ቦታዎችና የፖሊስጣቢያዎችን ጐብኝቷል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ እስርቤቶች በሺዎች የሚቆጠሩ ታሳሪዎችን ያካተቱ ጉብኝቶችን አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች፣ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች አባላት፣ እንዲሁም የሚዲያ ሰዎች የታሰሩባቸውን የፌደራል እስር ቤቶች ከመጐብኘት ታግደው ነበር፡፡ ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ የተባለ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (መያድ) የፌደራል እስር ቤቶችን ጨምሮ ብዙ እስር ቤቶች ውስጥ ስራውን እንዲሰራ ተፈቅዶለታል፡፡ በጊዜው ለዲፕሎማቲክ ሚሽኖችም በክልል እስር ቤቶችንና ታሣሪዎችን የእስር ቤት ባለስልጣናትን ቀደም ብለው ካሳወቁ እንዲያዩና እንዲያገኟቸው መንግሥት ይፈቅዳል፡፡ የአለማቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በተደጋጋሚና ቋሚ በሆነ ሁኔታ ሶስተኛ ወገን ሣይኖር እስረኞችን እንዲያነጋግር ፈቃድ አግኝቷል፡፡ የተጠረጠሩ የኦነግ ተዋጊዎች የታሰሩበትንም እስር ቤት እንዲጐበኝ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከብሄራዊ ደህንነት ጋር በተያያዘ የታሰሩ ኤርትራዊያን እና የኤርትራ ዘር ያላቸው ኢትዮጵያዊያንንም መጐብኘቱን ቀጥሎ ነበር፡፡

የመንግስት ባለስልጣናት በልዩ አቃቤ ህግ ቢሮ በጦር ወንጀልና በአሸባሪነት ተጠርጥረው የታሰሩ እውቅና ያላቸውን እስረኞች ዲፕሎማቶች እንዲጐበኟቸው የሚለጡትን ፈቃድ ቀጥለው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ባመቱ መጨረሻ በአዲስ አበባው ቃሊቲ እስር ቤት የሚገኙትንና በኖቬምበር 2005ቱ ፀረ መንግሥት ተቃውሞ ድርሻ ነበራቸው ተብለው የታሰሩትን የቅንጅት አመራሮች፣ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች አባላት እንዲሁም ጋዜጠኞች የአለም አቀፉ ማህበረሰብ ተወካዮች በተገደበ መልኩ እንዲጐበኟቸው ነበር መንግሥት የፈቀደው፡፡ እኒህኑ እስረኞች የፕሪዝን ፌሎውሺፕና የሃይማኖት መሪዎች እንዲጎበኟቸው ፈቅዶ ነበር፡፡

መ. በማን አለብኝነት ማስር ወይም ማቆየት

ምንም እንኳ ሕገ መንግሥቱና ሕጉ በማን አለብኝነት የሚፈፀሙ እስራትንና ማቆየትን ቢከለክሉም መንግስት ብዙውን ጊዜ እኒህን ህጐች አላከበረም ነበር፡፡

የፖሊስ የፀጥታው አካል ሚና

የፌደራሉ ፖሊስ ኮሚሽን ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሪፖርት ያደርጋል፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ደግሞ የፓርላማው ታዛዥ ነው፡፡ የክልል መንግሥት ሚሊሺያዎችም እንደ ክልላዊ ፀጥታ ሃይል ሲያገለግሉ ባብዛኛው ከፖሊሱና ከጦር ሰራዊቱ ውጪ ናቸው፡፡ ትናንሽ የሙስና ተግባራት በፖሊስ ሃይሉ ውስጥ ያሉ ችግሮች ሆነው ቀጥለው ነበር ፡፡ ይህም ችግር በዋናነት በትራፊክ ፖሊሶች አካባቢ የታየ ነበር፡፡ ከአሽከርካሪዎች ጉቦ ይቀበላሉ ፡፡ ማን አለብኝነትም ከባድ ችግር ሆኖ ቆይቷል ፡፡ መንግሥት በጣም በተወሰነ ደረጃ ነበር እኒህን ዓይነት ጥፋቶች በተመለከተ የተደረጉ የምርመራ ውጤቶችን ለሕዝብ ያቀርብ የነበረው፡፡ የፌደራሉ ፖሊስ ኮሚሽን ብዙ የፖሊስ ሃይል አባላት፤ የክልል ፖሊስን ጨምሮ፤ የሞያተኛነት ችግር እንደነበረባቸው አምኗል፡፡ በንግሥትም የፖሊሱንና የጦር ሰራዊቱን ምልምሎች ስለሰብዓዊ መብት ለማስተማር ጥረቱን ቀጥሏል ፡፡ ባመቱ ውስጥ መንግሥት የሰብዓዊ መብት ትምህርቱን ስርአተ ትምህርት ለማሻሻል እንዲሁም ከሕገ መንግሥቱና አለማቀፍ ሰብአዊ መብት ውሎችና ስምምነቶች ውስጥ ተጨማሪ ጉዳዮችን እንዲያካትት ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት የኘሪዝን ፌሎውሺኘ ማሕበርን፣ የአለማቀፍ ቀይመስቀል ኮሚቴንና የኢሰመጉን እርዳታ መጠየቁን ቀጥሏል፡፡

በኖቬምበር የአጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርቱን አቅርቧል ፡፡/ ክፍል 1 ሀን ይመልከቱ/

በቁጥጥር ስር ማዋልና ማሰር

በተደጋጋሚ የመንግሥት አካላት ያሉተገቢው የእስር ማዘዣ ሰዎችን ከማሰራቸውም ባሻገር ታሣሪዎች ጠበቆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው እንዳያገኟቸው ያደርጉ ነበር ፡፡ በተለይም ራቅ ባሉ ክልሎች ይህ ሁኔታ የከፋ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ሕጉ ማንኛውም ታሣሪ በተያዘ በ48 ሰዓታት ውስጥ የተመሰረተበት ክስ ሊነገረው እንደሚገባ ቢያስገድድም ባጠቃላይ ሲታይ ግን ይህ ሕግ ተግባራዊ አልተደረገም ፡፡ የዋስ መብት ቢኖርም ግድያ፤ ያገር ክህደትና ሙስናን ለመሣሠሉ ጥቂት የወንጀል ዓይነቶች ተፈፃሚ አልነበረም ፡፡ ባብዛኛው የመንግሥት አካላት በአንድ ሺህ ብርና በአስር ሺህ ብር መሃል ዋስ ያስጠራሉ ፡፡ ይህ ደግሞ ላብዛኛው ሕዝብ በጣም ውድ ነው ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፖሊስ ባለስልጣናት ፍርድ ቤት የሰጠውን በዋስ የመፈታት ውሳኔ ሁሌም አያከብሩም ነበር ፡፡ ፍርድ ቤት ካፀደቀው በከባድ ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ፖሊስ ምርመራ እስኪያካሂድ ለ14 ቀናት ሊታሰሩ ይችላሉ ፡፡ ለሌላ ተጨማሪ 14 ቀናትም ምርመራው ከቀጠለ በተጨማሪ ሊታሰሩ ይችላሉ፡፡ ሕጉም ማንም ሰው ከታወቀ እስር ቤት ውጪ እንዳይታሰር ያዛል ፡፡ ይሁን እንጂ በክልላዊ መንግሥት ሚሊሺያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ፡፡ በዛ ያሉ ያልታወቁ እስር ቤቶች ነበሩ ፡፡

ጠበቃ ገዝተው መከራከር ለማይችሉ ተከሳሾች መንግሥት የነፃ ጥብቅና አገልግሎት ያቀርባል፡፡ ይሄ የሚሆነው ግን ጉዳያቸው ለችሎት የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው ፡፡ ከችሎት በፊት ባለው የእስር ጊዜ ግን የመንግሥት አካላት ለታሣሪዎች ጥቂት የሕግ አገልግሎት ይፈቅዳሉ ፡፡ ከብዙ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በቀረቡ ሪፖርቶች መሰረት በትናንሽ ከተሞች የመንግሥት አካላት ሰዎችን በየፖሊስ ጣቢያዎቹ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለረጅም ጊዜያት ያስሩ ነበር፡፡ አንዳንዴም የነዚህ ሰዎች ደብዛ ለብዙ ወራት ይጠፋ ነበር ፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ብዙ ቅሬታዎችን ያቀርቡ ነበር ፡፡ ባመቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመንግሥት ሚሊሺያዎች ደጋፊዎቻችንን ያለምንም ክስ በተቃውሞ ሰልፎች በመሳተፋቸው ብቻ ይደበድቡና ያስሩ ነበር ብለዋል፡፡ (ክፍል 1 ሐ ን ይመለከቱ)

መንግሥት በመምህራን በተለይም በኦሮሚያ ክልል በሚገኙት ላይ የሚያደርገውን ወከባ ቀጥሎ ነበር ፡፡ ነፃው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር/ ኢመማ/ ባወጣው ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው የመንግሥት አካላት ብዙ

መምህራንን የኦነግ ደጋፊ ናችሁ በሚል ውንጀላ አስረዋቸዋል ። ብዙዎቹም ባመቱ መጨረሻም በእስር ቤት ነበሩ ።

ለምሣሌ በዲሴንበር ታዋቂ የሠራተኛ ማህበር አባላት የነበሩት ጥላሁን አያሌው ፤አንተነህ ጌትነት እና መቅጫ መንግሥቱ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለዋል። ጥቂቶች መምህራን ለብዙ ዓመታት ያለክስ ታስረው ነበር ። የሰብዓዊ መብት ታዛቢዎች ብዙዎች የተጓተቱ እስሮች ፖለቲካ ነክ ሣይሆኑ እንደማይቀር ይጠረጥራሉ ።

ፖሊስ ያለፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ በየሰው ቤት እየገባ ሰዎችን ማሰሩን ቀጥሎ ነበር ።(ክፍል 1ረ ን ይመልከቱ) በዚያ ዓመት ፖሊስ ጋዜጠኞችን አስሮ ነበር (ክፍል 2 ሀን ይመልከቱ) ሜይ 27 በሱቅ ባለቤቶችና በክልሉ ፖሊስ መካከል የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የናዝሬት ከተማ የፀጥታ ሃይሎች 180 ሰዎችን አስረው ብጥብጥ በማነሳሳትና ንብረት በማውደም ወንጀል ከሰዋቸዋል። (ክፍል 1 ሀን ይመልከቱ) በአመቱ መጨረሻም አብዛኛዎቹ ታሣሪዎች በነፃ የተለቀቁ ሲሆን እስር ላይ ስለቆዩት ሌሎች ታሣሪዎች ግን ምንም መረጃ አልነበረም።

ኦገስት 30 ቀን ኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኘው ጥቁር ኢንጪኒ ከተማ የፀጥታ ሃይሎች በአካባቢው በነበሩ የኦብኮ አባላት የተነሳሳ አመፅን ተከትሎ 250 ሰዎችን አስረው ነበር ። ባመቱ መጨረሻም 81 ሰዎች በእስር ቤት ሆነው የክህደት ክስ ተመስርቶባቸው ነበር ።

በማን አለብኝነት የመላው አማራ አንድነት ፓርቲ አባላትን በ2004 አስረዋል በተባሉ የአማራ ክልል ሚሊሺያዎች ፤ የወረዳ ባለስልጣናትና ፖሊሶች ላይ የመንግሥት አካላት ምንም እርምጃ አልወሰዱም ነበር ። በ2004 ያለምክንያት ታስረው የነበሩት የኦብኮ አባል ኦልባና ሌሊሳ በ2005 ተፈትተዋል።

በኖቬምበር 2005 የተቃውሞ ሰልፍ ተከልክሎ የነበረ በመሆኑ ፖሊስ ስብሰባ ወይም ትእይንተ ሕዝብ ያካሄዱ ሰዎችን ስለማሰሩ የቀረቡ ሪፖርቶች አልነበሩም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ በልዩ አቃቤ ሕግ ፅሕፈት ቤት የታሰሩ ሰዎች በፖለቲካ ምክንያት ነው ሲሉ ቢወነጅሉም፣ ይኸን ውንጀላ መንግሥት ያስተባብላል ። (ክፍል 1 "ሠ"ን ይመልከቱ)

በጃንዋሪ ወር አለማቀፍ የዜና አውታሮች የኖቬምበር 2005ቱን ከፍተኛ ፀረ መንግሥት ተቃውሞ ተከትሎ ታስረው የነበሩ ከ11,000 በላይ ሰዎች መለቀቃቸውን ዘግበው ነበር። ይሁን እንጂ ከምርጫው በኋላ የተከሰተውን ብጥብጥ የሚያጣራው አጣሪ ኮሚሽን ከ30,000 በላይ ሰዎች ታስረው እንደነበረ ሲገልፅ፣ ሌሎች ሪፖርቶች ደግሞ ይህ ቁጥር ከ50,000 በላይ ነበር ብለዋል። ከ2200 በላይ እስረኞች በነፃ ተለቀዋል ። ተጨማሪ በአዲስ አበባ ታስረው የነበሩ 734 ሰዎች በጥር ወር ተለቀዋል። ከ650 በላይ ከብጥብጡ ጋር በተያያዘ የተያዙ ሰዎች በጥር ወርም በዝዋይ ወህኒ ቤት ታስረው የነበረ ሲሆን ባመቱ መጨረሻም ሳይፈቱ የቀሩት ሰዎች እርግጠኛ ቁጥር አልታወቀም ነበር ።

በፌብሯሪ መጀመሪያ ላይ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ መንግሥት በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ በሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን አስሮ እንደነበር ገልጿል። ይህን ክስ መንግሥት ያስተባበለ ሲሆን 86 ተማሪዎች ብቻ በረብሻ፤ በንብረት ማውደምና "የመማር ማስተማሩን ሂደት በማስተጓጐል" ወንጀል የታሰሩ መሆኑን ገልጿል ።

አለማየሁ ፋንቱ የተባሉ ታዋቂ ነጋዴ በአክቶበር ወር የቅንጅትን ሰላማዊ ተቃውሞ ቀናት ካላንደር ይዘዋል በመባል ታስረው ነበር ። ከብዙ ሣምንታት እስር በኋላም በዋስ ተለቀዋል።

በሃያዎች የሚቆጠሩ የቅንጅት አመራሮች፤ የስነ ዜጋ ትምህርት በማስተማር የተሠማሩ መያዶች ብዙ አባላት እና ገለልተኛ ጋዜጠኞች በኖቬምበር 2005 እንደታሰሩ በዓመቱ መጨረሻም አልተፈቱም ነበር፡፡ (ክፍል 1 ሠን ይመልከቱ)

ከሜይ 2005ቱ የምክር ቤት ምርጫ በኋላ ታስረው የነበሩት ሁሉም የኦፌዴን አባላት ባመቱ መጨረሻ ተለቀዋል ፡፡ ከሶማሌያና ኬንያ በመነሳት ጥቃት ለሚያደርሱ ታጣቂ ተቃዋሚዎች ምላሽ ለመስጠት ጦር ሠራዊቱ ኦፕሬሽኖችን ማድረጉን ቀጥሎ ነበር ፡፡ እነዚህ ኦፕሬሽኖች አልፎ አልፎ በደቡብ፤ ሱማሌና ኦሮሚያ ክልሎች በማን አለብኝነት የሚፈፀሙ እስሮችን ያስከተሉ ነበሩ፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲና የኦብኮን አባላት በ2004 ያለምክንያት አስረው በነበሩት የአማራው ክልል ሚሊሺያዎች፤ የወረዳ ባለስልጣናትና ፖሊስ ላይ የመንግስት አካላት ምንም እርምጃ አልወሰዱም ነበር ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በ2004 በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተማሪዎችንና መምህራንን ለብዙ ሳምንታት የኦነግ ደጋፊ ናችሁ ብለው ባሰሩ ፖሊሶች ላይ መንግሥት ምንም ዓይነት እርምጃ አልወሰደም ነበር ፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር ላይ ቆይተዋል፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም ላመታት ያህል ነው የቆዩት ፡፡ የተወሰኑት እስረኞች ከኦነግ ጉዳይ ወይም በ2004 ተቀስቅሶ ከነበረው የተማሪዎች አለመረጋጋት ጋር በተያያዘ የታሰሩ የኦሮሞ ተማሪዎችና መምህራን ነበሩ ፡፡

መንግሥት ብዙዎችን ያለክስ በጎንደር እስር ቤት ማሰሩን ቀጥሎ ነበር ፡፡ የተወሰኑት ታሣሪዎችም ፖሊስ ጉዳያቸውን እስኪያጣራ ለዓመታት በእስር ቆይተዋል፡፡

ምህረት

በሴፕቴምበር 10 መንግሥት በ30 ዓመታት የመጀመሪያ የሆነውን ምህረት አድርጓል ፡፡ ይኸው በፌደራልና በክልል ይቅርታ ቦርዶች የተወሰነው ውሳኔ ለ10,000 እስረኞች መፈታት ምክንያት ሆኗል ፡፡ እነዚህ ግን ካጠቃላዩ የእስረኛ ቁጥር በግምት 15በመቶ ብቻ ነበሩ፡፡ ባጠቃላይ 237 እስረኞች ከፌደራሉ እስር ቤቶች በነፃ የተለቀቁ ሲሆን 11 የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው የነበሩ እስረኞችን ጨምሮ 26 እስረኞች ደግሞ ፍርዳቸው እንዲቃለልላቸው ተደርጓል ፡፡ የተቀሩት ከየክልሉ እስር ቤቶች ነበር የተፈቱት፤ 3,995 ከአማራ፤2,435 ከኦሮሚያ፤1,100 ከትግራይ፤ በግምት 2,400 ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፤ እንዲሁም 43 እስረኞች ደግሞ ከጋምቤላ ክልል እስር ቤቶች

ተፈትተዋል ፡፡ ይህ ምህረት በአስገድዶ መድፈር እና በሙስና ወንጀሎች የተፈረደባቸውን እስረኞች አላካተተም ፡፡

ሠ. ሚዛናዊና ግልፅ የፍርድ ሂደትን መከልከል ፡

ሕጉ ነፃና ገለልተኛ የፍትሕ አካላት እንዲኖሩ ቢያዝም ፍርድ ቤቶች ደካማና ብዙ የሥራ ጫና ያለባቸው ሆነው ቆይተዋል፡፡ የፖለቲካ ጫናም ያለባቸው ሆነው ታይተዋል፡፡

መንግሥት በወረዳ፤ በዞንና ክልል ደረጃዎች ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም የፍትሕ አካላትን አደረጃጀት በፌደራል አሰራር መሠረት እንደገና ማዋቀሩን ቀጥሏል፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ህግን፣ በክልሎች መሀከል ያሉ የህግ ሂደቶችን፣ እንዲሁም የሀገርን ደህንነት የሚመለከቱ አዲስና የይግባኝ ጉዳዮችን ተመልክተው ይፈርዳሉ፡፡ የየክልሉ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ራሳቸውን ችለው ብዙውን ጊዜ ክልላዊ ጉዳዮችን ያዳምጣሉ፡፡

በየክልሉ ያሉ የፌደራሉ የፍትሕ ሚኒስቴር ቢሮዎች የየክልሉን የፍትሕ ሂደት ይቆጣጠራሉ፡፡ ጥቂት የክልል ፍርድ ቤቶች በክልላዊም ሆነ በፌደራል ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ነበራቸው፡፡ ይህም የሚሆነው በዚያ ክልል የፌደራል ፍርድ ቤቶች በሌሉ ወቅት ነው፡፡ ባጠቃላይ የፌደራሉ የፍትህ አካላት በየክልሉ በተወሰነ ደረጃ ነው የሚገኙት፡፡ ውሱን መረጃዎች፡ አንዳንድ የመነግሥት የክልል ባለስልጣናት ለማንም ከፍ ላለ ባለስልጣን አካል ተጠያቂ ነን ብለው እንደማያምኑ ያስረዳሉ፡፡ የክልሎች ህግ እስኪፀድቅ ድረስ ግን ሁሉም ዳኞች የፌደራል መንግሥት ባወጣቸው ህጐች ይመራሉ፡፡

በፍትህ አካላቱ ውስጥ ያለውን ስር የሰደደ የተማረ የሠው ኃይል እጦት ለመቀነስ፣ ምንም እንኳን የደመወዙ መጠን ብዙ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን የሚስብ እንዳልሆነ ባለስልጣናቱ ቢረዱም፣ መንግሥት ከዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞችና አቃቢያነ ህግን እየመረጠ ማሠልጠኑን ቀጥሎ ነበር፡፡

የፍርድ ሂደት ሥነ ሥርአቶች

በህጉ መሠረት በወንጀል የተጠረጠሩ ሠዎች ነፃና ግልፅ በሆነ ፍርድ ቤት ጉዳያቸው ጊዜ ሳይፈጅ ሊታይ ይገባዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ ግለሰብ በፍርድ ቤት ወንጀለኛ እንደሆነ ካልተረጋገጠበት በስተቀር ነፃ የመሆን፣ በመረጠው የሕግ ባለሙያ የመወከል እና ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ይህ ሁሉ ጥበቃ ቢኖርም ቅሉ ዝግ ችሎቶች የተደረጉ ሲሆን በዚህ ወቅትም የመንግሥት አካላት ለተከሳሾቹ ምንም ዓይነት የህግ ምክር እንዳያገኙ የከለከሉበት ጊዜ ነበር፡፡ (ክፍል 1 መን ይመልከቱ) እስረኞችም ሣይፈረድባቸው ወንጀለኛ ይባሉ ነበር፡፡ የሕዝብ ጠበቆች ቢሮ በጣም ድሃ ለሆኑ ሰዎች የህግ አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም በተለይ የልዩ አቃቤ ሕግ ቢሮ በሚያቀርባቸው ክሶች ላይ የሚሠጠው አገልግሎት በጣም ውሱን ነበር፡፡ ምንም እንኳን በሙስና የሚከሰሱ ሰዎች የቀረቡባቸውን መረጃዎች ከፍርድ ሂደቱ በፊት እንዲመለከቱ ህጉ በግልፅ ቢያስቀምጥም የመንግሥት አካላት የተከላካይ ጠበቆች እኒህን ማስረጃዎች እንዳያገኙ ይከለክሉ ነበር፡፡

ህጉ ቀደም ሲል ለነበሩ የሃይማኖትና ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ህጋዊ ዕውቅና በመስጠት የፌደራልም ሆነ የክልል ህግ አውጪዎች ለነዚሁ ፍርድ ቤቶች እውቅና እንዲሰጧቸው ይፈቅዳል፡፡ በህጉ መሠረት የባህልም ሆነ የሃይማኖት ፍርድ ቤቶች እንዲሰየሙ በጉዳዩ የሚወዛገቡት አካላት በነኚህ አይነት ፍርድ ቤቶች ጉዳያቸው እንዲታይ መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ የሸሪአ ፍርድ ቤቶች ሃይማኖታዊና ቤተሰባዊ የሆኑ የሙስሊሞችን ጉዳዮች ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ባሕላዊ የህግ መንገዶች፣ እንደሽምግልና ኮሚቴ ያሉት፣ ሥራቸውን ቀጥለው ነበር፡፡ በሕግ የተቀመጠ ባይሆንም እነኚህ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የብዙሃኑንና ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቅርበት የሌላቸውን በገጠር የሚኖሩ ሕዝቦች ጉዳዮች ሲፈቱ ቆይተዋል፡፡

የፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰባተኛ የወንጀል ችሎት በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርሱ የወሲብ ጥቃት ወንጀሎችን ጉዳይ ይመለከታል፡፡

ሦስት የፌደራል ዳኞች በአንድ ችሎት ተሰይመው የወጣት አጥፊዎችን ጉዳይ ይመለከታሉ፡፡ ብዙ ሲንከባለሉ የቆዩ የወጣት ጥፋተኞች ጉዳዮች ነበሩ፡፡ በመሆኑም ጉዳያቸው እስኪታይ ድረስ ብዙ ወጣት ጥፋተኞች ከአዋቂዎች ጋር ታስረው ይቆያሉ፡፡

የጦር ሰራዊቱ የፍትህ ሥርአት በየወቅቱ እያደገ የመጣውን ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ሊያዩ የሚችሉ ዕወቀት ያላቸው ሠራተኞች የሉትም፡፡ ባመቱም የጦር ሰራዊቱን የፍትህ ባለስልጣናት ለማሰልጠን የሚያስፈልገው የውጪ ዕርዳታ ቀጥሎ ነበር፡፡

በዲሴንበር 12 ቀን ከ12 ዓመታት የፍርድ ሂደት በኋላ 57 ዋና ዋና የቀድሞ ደርግ ባስልጣናት፣ የቀድሞውን ኮሚኒስት አምባገነን ኮሎኔል መንግሥቱ ሃይለማርያምን ጨምሮ፣ በተከሰሱበት በዘር ማጥፋት፣ በሃገር ክህደት

እና በግድያ ወንጀሎች ወንጀለኛ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ 27ቱ (መንግስቱና ሌሎች 26 ግለሰቦች) ካገር በመኮብለላቸው ጉዳያቸው በሌሉበት ታይቷል፡፡ ባመቱ መጨረሻም የቅጣት ውሳኔ እየተጠባበቁ ነበር፡፡ በሪፖርት ማድረጊያ ጊዜው መጨረሻ ፍርድ ቤቶች ከደርግ ወንጀል ጋር ግንኙነት በነበራቸው 1018 ሰዎች ላይ የፍርድ ውሳኔ ሰጥተው ነበር፡፡ ከ5,000 እስከ 6,000 የሚያህሉ ሌሎች ተከሳሾች ደግሞ ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ነበረ፡፡

የፖለቲካ እስረኞች

ባመቱ ባጠቃላይ የነበሩት የፖለቲካ እስረኞች ቁጥር በመቶዎቹ ተገምቷል፡፡ የቅንጅት አመራሮች፣ የሲቪል ማህበረሰቡ አባላት፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች እንዲሁም ጋዜጠኞች የኖቬምበር 2005 ቱን ተቃውሞ ተከትሎ የታሠሩ ሲሆን ባመቱ መጨረሻም ባገር ክህደት፣ በዘር ማጥፋት ሙከራ እንዲሁም ሕገ-መንግስቱን በመፃረር ወንጀሎች ተከሰው በፍርድ ሂደት ላይ ነበሩ፡፡ ክሶቹ ከባዶች በመሆናቸው እስከሞት በሚደርስ ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው፡፡

ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ከነበረው ሰዎች ውስጥ ለአዲስ አበባ ከንቲባነት ተመርጠው የነበሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት የሩዋንዳ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ የበሩት ዶክተር ያዕቆብ ኃ/ማርያም፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ የአክሽን ኤይድ ተወካይ አቶ ዳንኤል በቀለ፣ አቶ ነዋነት በቀለ፣ የፌደራል ፓርላማ አባል የነበሩት አቶ ክፍሌ ጥግነህ እንዲሁም ሌሎች ይገኙበታል፡፡ እድሜያቸው ከ18 እስከ 76 የሆነ ወደ 200 ገደማ ተከሳሾች ባራት በተለያዩ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ክስ ተመስርቶባቸው ነበር፡፡ ቀደም ሲል ከተከሰሱት ውስጥ አምስት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጋዜጠኞች የነበሩ ቢሆንም ባለም አቀፍ ጫና ምክንያት ክሳቸው ተነስቷል፡፡

በአዲስ አበባ የፍርድ ሂደታቸውን እየተከታተሉ ያሉት 200 የፖለቲካ እስረኞች ባብዛኛው ባሳዛኝ ሁኔታ በቃሊቲና በከርቸሌ እስር ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በመጋቢት ወር የቅንጅት ዋና ፀሐፊ የሆኑት አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል በከርቸሌ እስር ቤት ብቻቸውን ባንድ ክፍል ተዘግቶባቸው እንዲታሠሩ ተደርጓል፡፡ በነሐሴ ወርም ሌላው የቅንጅት አባል አቶ አንዱአለም አራጌ ከጋዜጠኞቹ ሲሳይ አጌና እና እስክንድር ነጋ ጭምር ብቻቸውን ባንድ ክፍል ተዘግቶባቸው እንዲታሠሩ ተደርጓል፡፡

ብዙዎቹ የፖለቲካ እስረኞች በታሠሩበት ወቅት ከባድ የጤና ችግሮች አጋጥመዋቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ወደልዩ የእስር ቤት ሆስፒታል ተወስደው ዕርዳታ ከተደረገላቸው በኋላ ወደ እስር ቤታቸው ተመልሰዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ምንም ዓይነት የህክምና አገልግሎት አላገኘንም ሲሉ አማረዋል፡፡ ባመቱ ነፍሰጡር የነበረችው ጋዜጠኛ ሰርክዓለም ፋሲል በቃሊቲ ታስራ ባለችበት ወቅት ከቀኗ ቀድማ ተገላግላለች፡፡ ልጇን ለማጥባት ሆስፒታል መቆየት ፈልጋ ተከልክላለች፡፡ የልጁ አባት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋም ባንድ ክፍል ለብቻው ተዘግቶበት ታስሮ ስለነበር ልጁን ማየት አልቻለም ነበር፡፡

የፖለቲካ እስረኞቹ ቤተሰቦች እንደገለፁት እስረኞቹ በቂ ብርሃን እንዳያገኙ ከመደረጋቸውም በላይ ፍራሽም ሆነ በቂ የመታጠቢያ ሥፍራዎች የሏቸውም ነበር፡፡ ባመቱ ውስጥ ብዙ ተከሳሾችና ቤተሰቦቻቸው የጉብኝት መብታቸው እንደተገደበባቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲያማርሩ ነበር፡፡ ባንድ እስር ቤት ታስረው ካሉ ሌሎች እስረኞች በተለየ የፖለቲካ እስረኞች የጉብኝት መመሪያ በጣም የተወሰነ ነበር፡፡ አለም አቀፉ የቀይ መስቀል ኮሚቴ እንኳን ቋሚ የጉብኝት ፈቃድ ተከልክሎ ነበር፡፡ (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)

ፍትሐብሔር ህግና ማሻሻያዎቹ

ህጉ ዜጐች በፍትሐብሔር ችሎቶች የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ይግባኝ እንዲሉ መብት የሰጠ ቢሆንም ባመቱ ምንም ዓይነት የጥሰት ጉዳዮች አልተመዘገቡም ነበር፡፡ በተጨማሪም በፓርላማው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዲከታተልና እንዲመዘግብ የተቋቋመው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከግለሰቦች ለሚቀርቡ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቅሬታዎች ምላሽ እንዲሰጥ የተቋቋመ ቢሆንም ባመቱ መጨረሻ ኮሚሽኑ ይህንን አቅም አላዳበረም ነበር፡፡

ረ. የግለሰባዊ ህይወትን፣ ቤተሰብን፣ ቤትን ወይም ግንኙነትን ያለምክንያት መድፈር

ህጉ ባለስልጣናት የማንንም የግል ንብረት ለመበርበር የፍርድ ቤት ማዘዣ እንዲኖራቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በተግባር የሚታየው፣ በተለይም ከአዲስ አበባ ውጪ፣ ፖሊስ ያለፍርድ ቤት ማዘዣ የግለሰቦችን ንብረት ሲበረብር ነበር፡፡ (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)፡፡ እንደተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች ገለፃ ፖሊሶች አንዳንዴ ሐሰተኛ የፍርድ ቤት ማዘዣዎችን በመጠቀም ገንዘብ እስከመቀበል ድረስ የሚደርሱ ወንጀሎችን ይፈፅማሉ፡፡ ባመቱ መጨረሻ የተጭበረበሩ የፍርድ ቤት ማዘዣዎችን ጭምር በመጠቀም የፌደራሉ ፖሊስ አባላት ግለሰቦችን መዝረፋቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡

ፖሊስ በነፃ ዜጐች ቤት በሃይል እንደሚገባ የሚገልፁ ሪፖርቶች ቀጥለው ነበር፡፡

በፀረ መንግስት ተቃውሞው ወቅትና ከተቃውሞው በኋላ፣ በሰኔ እና በኖቬምበር 2005፣ የፀጥታ ሃይሎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤቶችን በርብረዋል፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን በእኩለ ሌሊት ከቤታቸው ወስደዋል፤ እንዲሁም ባብዛኛው ቤተሰቦቻቸውንና ሌሎች ነዋሪዎችንም አስረዋል፡፡

ቀደም ባሉት ዓመታት ከነበረው በተለየ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የመንግስት አካላት ቤታቸውን እንዳቃጠሉና ቢሮዎቻቸውን እንደዘረፉ ሪፖርት አላደረጉም፡፡

ሁሉም የሞገድ መገናኛ መንገዶች በመንግስት ቁጥጥር ስር ነበሩ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የስልክ ጠለፋና ሌሎች ተመሳሳይ ተሸሽጎ የማዳመጥ ተግባራት እንደተፈፀሙ ሪፖርት አድርገዋል፡፡

መንግስት ሰፊ የሆነ የመረጃ ዘዴ ይጠቀም ነበር፡፡ ክፍያ በሚደረግላቸው መረጃ አቀባዮች ስለ ተወሰኑ ሰዎች መረጃ ይቀበል ነበር፡፡

በአመቱ ውስጥ በገጠር በግድ የተፈናቀሉ ቤተሰቦች እንደነበሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ መንግሥት ሰዎችን በድርቅ ከተጠቁ ቦታዎች ወደለም ስፍራዎች የማስፈሩ ፕሮግራም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነበር ቢልም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን የየክልሉ ባስልጣናት ባንዳንድ የገጠር ከተሞች ላይ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ያነጣጠረ ማፈናቀል አድርገዋል ሲሉ ይከሳሉ፡፡ የሚዲያ ዘገባዎች እንደጠቆሙት ብዙውን ጊዜ መንግሥት ሰፋሪዎቹን ምንም ዓይነት መሠረተ ልማት ወይም ንፁህ የመጠጥ ውሃ በሌለባቸው ቦታዎች በማስፈሩ ከወትሮው የተለየ የህፃናት ሞት ተከስቷል፡፡

ባመቱ ውስጥ ከኢሰመጉና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚወጡ ታማኝ ሪፖርቶች ቀጥለው ነበር፡፡ እነዚህ ሪፖርቶችም ባንዳንድ የኦሮሚያ፣ የአማራና የደቡብ ክልሎች ቦታዎች የመንግሥት ባለስልጣናት፤ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲሉ በመሬት ድልድል፣ የዕርዳታ እህል በመከልከልና ማዳበሪያ በመንፈግ ያስፈራሩ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ የገዢው ፓርቲ ወይም የመንግሥት ሰዎች ግለሰቦችን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንዳይሆኑ ወይም ለተቃዋሚዎች ቤት እንዳያከራዩ ያዋክቧቸው እንደነበር የሚገልፁ ብዙ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ላይ ያተኮሩ ድብደባዎች፣ ቤት ቃጠሎዎችና ግድያዎች በተለያዩ ያገሪቱ ክፍሎች ይደረጉ እንደነበር የሚጠቁሙ ብዙ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ (ክፍል 1ሐና 1መን፤ 3 እና 5ን ይመልከቱ)

መምህራንና ሌሎች የመንግስት ሠራተኞች የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በመሆናቸው ብቻ የሥራ ውላቸው ይቋረጥ እንደነበር የሚገልፁ ታማኝ ሪፖርቶችም ነበሩ፡፡ እንደተቃዋሚው ፓርቲ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴን) የክልሉ መንግሥት የደኢሕዴን አባላትን፣ በተለይም አስተማሪዎችን፣ ከስራ ማባረሩን ቀጥሎ ነበር፡፡

ከፍቺ ወይም ከትዳር ጓደኛ ሞት በኋላ ማንም ሰው በድጋሚ ማግባት ቢፈልግ ስድስት ወር መጠበቅ እንደሚኖርበት ህጉ ያዛል፡፡ (ክፍል 5ን ይመልከቱ) መንግሥት ይህ ስድስት ወር የመቆያ ጊዜ ሴቷ ከቀደመው ባሏ ልጅ ፀንሳ ይሁን አይሁን ለመወሰን በግድ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል፡፡ በተግባር ግን ተፈፃሚ ሆኖ አያውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ጋብቻውን የሚያፀድቀው አካል የእርግዝና ምርመራ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ማንም ይመለከተኛል የሚል አካል ጋብቻው ለምን በመቆያው ወቅት እንዲፈፀም እንደተፈቀደ በፅሁፍ ማብራሪያ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡

የፀጥታ ሃይሎች በመንግሥት ለጥያቄ የሚፈለጉ ግለሰቦችን ቤተሰቦች ማሠራቸውን ቀጥለው ነበር፡፡